# የኮሎራዶ የአካዳሚክ ስኬት መለኪያዎች

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበባት እና የሂሳብ ውጤት ሪፖርቶችን መረዳት

www.cde.state.co.us




**የተማሪዎን የውጤት ሪፖርት ለማየት የቤተሰብ ፖርታልን ይጎብኙ Family Portal ።**
ሪፖርቱን እንዴት ማንበብ እንደሚቻል የሚያብራራ እና ስለተማሪዎ የስራ አፈጻጸም ደረጃ መረጃ የሚሰጥ ቪዲዮ ለማየት በተማሪዎ የአፈጻጸም ሪፖርት አናት ላይ ያለውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ፡ቪድዮዉን ይመልከቱ .

## የተማሪዎን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበባት እና የሂሳብ ውጤቶች ሪፖርቶችን እንዴት ማንበብ እንደሚችሉ - ገጽ 1




1 **የተማሪ አፈጻጸም አጠቃላይ እይታ** - ተማሪዎች ከአራቱ የአፈጻጸም ደረጃዎች በአንዱ የሚወድቅ አጠቃላይ የቁጥር ነጥብ ይቀበላሉ፡ ገና የሚጠበቁትን መስፈርት ያላሟሉ፣ የሚጠበቁትን መስፈርት በከፊል ያላሟሉ፣ የሚጠበቁ መስፈርቶችን ያሟሉ ፣ ወይም የሚጠበቁትን መስፈርቶች በላይ ሰርተዋል የሚሉት ናቸው የመቶኛ ደረጃው ተማሪዎ ከሌሎች የኮሎራዶ ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር ምን ያህል ጥሩ ስራ እንዳከናወነ ያሳያል። ለምሳሌ፣ በ69ኛ ፐርሰንታይል ውስጥ ያለ ተማሪ በክልሉ ውስጥ ካሉ ተማሪዎች ከ69 በመቶ በላይ የተሻለ አፈጻጸም አሳይቷል።

2 **የአፈጻጸም ደረጃዎች** - የአፈጻጸም ደረጃዎች ተማሪዎች በክፍላቸው ደረጃ የሚጠበቁትን እንዴት በሚገባ እንዳሟሉ ይገልፃሉ። እያንዳንዱ የአፈጻጸም ደረጃ በተለያዩ ውጤቶች ይገለጻል። ከፍተኛዎቹ ሁለት የስራ አፈጻጸም ደረጃዎች ተማሪዎች የሚጠበቁትን እንዳሟሉ ወይም ማለፋቸውን እና ለሚቀጥለው ክፍል ደረጃ ላይ መሆናቸውን ያመለክታሉ። ዝቅተኛዎቹ ሶስት የስራ አፈጻጸም ደረጃዎች ተማሪዎች በክፍል ደረጃ የሚጠበቁትን ሙሉ በሙሉ እንዳሟሉ አላሳዩም።

3 **የውጤት ክልል** - የአልማዞች ቅርጾች በግራፉ ላይ የልኬት ውጤቶችን ይወክላሉ። በተማሪዎ አልማዝ ዙሪያ ያሉ ቀስቶች ፈተናው ብዙ ጊዜ ከተወሰደ ተማሪዎ ሊያገኝ የሚችለውን የውጤት ክልል ያሳያሉ፤በምሳሌው የተማሪው አልማዝ ዙሪያ ያሉ ቀስቶች ፈተናው ብዙ ጊዜ ቢወሰድ ተማሪው በተመሳሳይ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ማስቆጠር ይችል ነበር።

4 **አጠቃላይ የውጤት ንጽጽር** - ትምህርት ቤት፣ ድስትርክት እና የግዛት አልማዝ ከልጅዎ ጋር ተመሳሳይ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች አማካኝ ነጥቦችን ይወክላሉ፣ ይህም የልጅዎ ውጤት ከሌሎች እነዚህን ፈተናዎች ከወሰዱ ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር ለማየት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በዚህ ምሳሌ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤቱ ያነሰ እና ከዲስትሪክቱ እና ከግዛቱ የላቀ ውጤት አስመዝግቧል። የተማሪን ግላዊነት ለመጠበቅ፣ አነስተኛ የተማሪ ብዛት ላላቸው ትምህርት ቤቶች እና ወረዳዎች ውጤቶች አይታዩም።

5 **የስቴት አፈጻጸም** - የተሳትፎ መረጃ የትምህርት ቤት፣ የዲስትሪክት እና የስቴት-ደረጃ ውጤቶችን ትርጉም እንዲሰጡ ይረዳዎታል። ከአጠቃላይ የአፈጻጸም ግራፊክ በታች ያሉት መስመሮች በእያንዳንዱ የአፈጻጸም ደረጃ ያከናወኑትን ተማሪዎች መቶኛ ያሳያሉ። የተሳትፎ መጠን ዝቅተኛ ሲሆን የት/ቤት፣ የዲስትሪክት እና የክልል አፈፃፀም ትርጓሜዎች በጥንቃቄ መደረግ አለባቸው።




**የግራፍ ቁልፍ** - በገጽ ሁለት ላይ ያለው ቁልፍ በሪፖርቱ የውጤት ክፍፍል ክፍል ውስጥ የትኛው መስመር  የተማሪዎን አፈጻጸም፣ የዲስትሪክት አፈጻጸም እና የስቴት አፈጻጸምን ያሳያል። የደመቀው  ቋሚ መስመሮች መስፈርቱን አሟልቷል የሚለዉን  የአፈጻጸም ደረጃ መነሻ ነጥብን ይወክላሉ።

**የንባብ አፈጻጸም** - አጠቃላይ የንባብ ውጤቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት ዘገባዎች በግራፉ ላይ ባሉ አልማዞች ይወከላሉ። በተማሪዎ አልማዝ ዙሪያ ያሉ ቀስቶች ምዘናው ብዙ ጊዜ ከተካሄደ ተማሪዎ የሚያገኘውን የውጤት ክልል ያሳያሉ። የልጅዎ የንባብ ውጤት ከሌሎች ፈተናዎች ጋር ሲነጻጸር እንዴት እንደሆነ ለማየት የትምህርት ቤቱን፣ የዲስትሪክቱን እና የግዛቱን ውጤቶች እና አልማዞችን ይመልከቱ። በዚህ ምሳሌ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤቱ ትንሽ ያነሰ እና ከዲስትሪክቱ እና ከግዛቱ ከፍ ያለ ውጤት አስመዝግቧል። በምሳሌው የተማሪው አልማዝ ዙሪያ ያሉ ቀስቶች ፈተናው ብዙ ጊዜ ከተወሰደ ተማሪው ከትምህርት ቤቱ ጋር ተመሳሳይ ወይም የበለጠ አስቆጥሮ ሊሆን ይችላል። ማሳሰቢያ፡ የንባብ ንዑስ አፈጻጸም ውጤቶች ከአጠቃላይ ነጥብ በተለየ ሚዛን ላይ ናቸው።

**የውጤት ማብራሪያ** - ይህ ክፍል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበባት ዘገባ እና በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ በሂሳብ ዘርፎች ላይ በተወሰኑ የንባብ እና የመጻፍ ቦታዎች ላይ የተማሪዎትን አፈፃፀም ዝርዝር ያቀርባል። ተማሪዎ የት ላይ ጥሩ ውጤት እንዳለው  ወይም የት ላይ  መሻሻል እንዳለበት ማየት ይችላሉ። በእነዚህ ዘርፎች ያለው አፈጻጸም ተማሪዎ በእያንዳንዱ ምድብ ምዘና ላይ እንዳገኛቸው የነጥብ መቶኛ ሪፖርት ተደርጓል። የተማሪዎን አፈጻጸም ከዲስትሪክት እና ከስቴት አማካዮች እንዲሁም መስፈርቱን አሟልቷል በሚለው  የሚጠበቁ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ካሉ ተማሪዎች ጋር ለማነፃፀር በገጹ አናት ላይ ባለው የግራፍ ቁልፍ ላይ የተገለጹትን መስመሮችን  ይጠቀሙ። በዚህ ምሳሌ፣ በንባብ መረጃ ጽሑፍ እና መዝገበ ቃላት ምድብ ተማሪው ከዲስትሪክቱ እና ከግዛቱ በልጦ ነበር። ተማሪው በንባብ ሥነ-ጽሑፍ ጽሁፍ ምድብ ውስጥ እንደ ድስትርክቱ ፣ ክፍለ ሀገር ወይም ተማሪዎች በመስፈሩን ያሟላል በሚለው አፈጻጸም ደረጃ ጥሩ ውጤት አላስገኘም። ማስታወሻ፡ በመቶኛ የተገኙ ነጥቦች በዓመታት ሊነጻጸሩ አይችሉም።

## የበለጠ የት መማር እችላለሁ?

April 2025

ኮሎራዶ የአካዳሚክ ስኬት መለኪያዎች (CMAS) ፈተናዎች ለሁሉም የኮሎራዶ ተማሪዎች የሚሰጡ ግምገማዎች ብቻ ናቸው።
በእያንዳንዱ ክፍል መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸውን እና ማድረግ የሚችሉትን በሂሳብ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት፣ በሳይንስ እና በማህበራዊ ጥናቶች ይለኩ። የበለጠ ለማወቅ፡ www.cde.state.co.us/communications/resourcesforparents ይጎብኙ